ትምህርተ ፡ ኅቡአት ።

፩ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አሜን

በእንተ ፡ ትምህርተ ፡ ኅቡአት ።

፪ ፡ ለምዕመናን ፡ ሥውር ፡ የነበረ ፡ ከክርስቶስ ፡ መገለጽ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ቊርባን ፡ በፊት ፡ የሚነገር ፡ የሚነበብ ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ትምህርት ፡ የሚጸለይ ፡ መለኮታዊ ፡ ምስጋና ትምህርተ ፡ ኅቡአት ፡ ይህ ፡ ነው ። ይኸውም ከመጽሐፈ ፡ ኪዳን ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፡ ከሰባቱ ፡ ኪዳናት ፡ አንዱ ፡ ነው ።

፫ ፡ ዕለ ፡ ትምህርተ ፡ ኅቡአት ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ እንናገራለን ፡ እናስተምራለን ፡ እንደዚህም ፡ እያልን ፡ እንጸልያለን ።

፬ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረው ፡ [illegible]ሬም ፡ ያለው ፡ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ ለዘ[illegible]ለም ፡ የሚኖረው ፡ ለኩነተ ፡ ሥጋ ፡ [illegible]ጣው ፡ ዳግመኛም ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡

ለማሳለፍ ፡ የሚመጣው ፡ በለበሰው ፡ ሥጋ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሲል ፡ የታመመው ፡ በሞቱ ፡ ፃዕረ ፡ ሞትን ፡ ያጠፋው ፡ የተቀበረው ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሙታን ተለይቶ ፡ የተነሣው ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

፭ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕይወትነት የአዳምን ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይ ፡ አድርጎ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ ያለመለወጥ ፡ በመለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

፮ ፡ መዋቲ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ያደረገው ፡ ያከበረው ፡ ሞትን ፡ በሥጋ ፡ ድል ነስቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረገው ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን በኛ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሠልጥኖ ፡ የነበረ ፡ ዲያብሎስን ፡ የሥልጣን ፡ ወጥመድ ፡

የበጣጠሰና ፡ ኃይሉን ፡ የሚያሳይበት የፍዳን ፡ ቁራኝነት ፡ ያጠፋ ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

፯ ፡ በመወለድ ፡ ሥልጣን ፡ ከሃሊነት ያለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከድንግል ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ ወገኖቹን ፡ ለማውጣት ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ ባየው ጊዜ ፡ ጨለማን ፡ የተጐናጸፈ ፡ ዲያብሎስ ፡ ፈራ ፡ ደነገጠ ።

፰ ፡ በማይለይ ፡ በማይነጠል ፡ ምክር በአንዲት ፡ ፈቃድ ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ ሰማያትን ፡ የፈጠረ ፡ እርሱ ፡ ከአባቱ ፡ ጋር የመላእክት ፡ አክሊላቸው ፡ ነው ፡ ለመላእክት ፡ አለቆችም ፡ ኃይላቸው ፡ የሆነ የኃያላን ፡ ፈቃዳቸው ፡ ለአጋዕዝትም ፡ የረቂቅነታቸው ፡ ርቀት ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ መንግሥት ፡ ያለችውና ፡ የቅዱሳንም ፡ ገዢያቸው ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

፱ ፡ የማይመረመር ፡ የአብ ፡ ኅሊና ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ የአብ ፡ ጥበብ ፡ እርሱ ነው ፡ የአብ ፡ ኃይሉ ፡ ቀኝ ፡ እጁ ፡ ልዑል ፡ ክንዱ ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

፲ ፡ በቅድምናው ፡ የነበረ ፡ መሆኑን ፡ አምነን ፡ በሥጋ ፡ ተገልጾ ፡ የደኅንነታችን ፡ መገኛ ፡ እንደመሆኑ ፡ ለሱ ፡ እንገዛለን ፡ ከክፉ ፡ የሚሠውረን ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ የሚረዳን ፡ በጥቃታችን ፡ የሚደርስልን ፡ ጌታ ፡ ፍጹም ፡ ዋጋን ፡ የሚሰጥ ፡ አምባ ፡ መጠጊያችን ፡ በቸርነት ፡ የሚጠብቀን ፡ በረድኤት ፡ የማይለየን ፡ በሃይማኖት ፡ የሚያጸናን ፡ ጠላት ፡ የማይደፍረው ፡ ጽኑ ፡ ቅጽራችን ፡ የደስታ መገኛ ፡ መግቢያ ፡ መውጫ ፡ በራችን ፡ የመ ሕይወትን ፡ የሚያድል ፡ ምግባችን ፡ የመንፈስ ፡ ርካታን ፡ የሚሰጥ ፡ መጠጣችን ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

፲፩ ፤ የተወለደ ፡ እንጂ ፡ ያልተፈጠረ ፡
የሚወስነው ፡ የሌለ ፡ እሱ ፡ በድንግል ፡
ማኅፀን ፡ የተወሰነ ፡ ኃጢአት ፡ ሳይኖር
በት ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ የኛን ፡ ኃጢአት ፡
ተሸክሞ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ የወጣ ፡ የሞ
ተው ፡ እርሱ ፡ ሕያው ፡ እንደሆነ ፡ የም
ናምንበት ፡ ከአባቱ ፡ ዕሪና ፡ ያልተለየ ፡
የአብ ፡ ልጁ ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ነው ።

፲፪ ፡ ከላይ ፡ በልዕልና ፡ ካለ ፡ ከአብ ፡
አንድነት ፡ ሳይለይ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡
በሥጋው ፡ በተቀበለው ፡ መከራ ፡ ያዳ
ነን ፡ ሀብተ ፡ ንጽሕ ፡ ሀብተ ፡ ሕይወት ፡
የሚሆን ፡ የሚያድን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን
ያደለን ፡ በማየ ፡ ጥምቀት ፡ ከኃጢአት
ነፃ ፡ ያደረገን ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ነው ።

፲፫ ፤ እርሱ ፡ ለዘላለሙ ፡ አድር
ባቸው ፡ የሚኖር ፡ ሲሆን ፤ በሚፈሩት ፡

ሰዎች ፡ ልቡና ፡ አድሮ ፡ የዕውቀትን ፡
ብርሃን ፡ የሚያበራ ፡ ሰይጣን ፡ ከሚሄ
ድበት ፡ የተንኮል ፡ ጐዳና ፡ ሁሉ ፡ እንድን
ለይ ፡ ጥበበኞች ፡ የሚያደርገን ፡ ነፍሳችንን
ከባሕረ ፡ ሲኦል ፡ የሚያሻግር ፡ ከዘመናት
ሁሉ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ሁላችን ፡ የምና
ምንበት ፡ አምላክ ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ አብ ፡ ጋር ፡ ለዘለዓለም
ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ እሱ ፡ ከምትናደድ ፡
ኅሊና ፡ የተነሣ ፡ ስሕተት ፡ ባመጣው
ጠንቅና ፡ አእምሮ ፡ በማጣት ፡ ዓለም ፡
በፍዳ ፡ ተይዞ ፡ ሲንገላታ ፡ ባየው ፡ ጊዜ
ባሕርየ ፡ ሰብእን ፡ ሊያድን ፡ ወዶ ፡ በሰ
ማይ ፡ ካሉ ፡ መላእክት ፡ ተሠውሮ፣ ከድ
ንግል ፡ ማኅፀን ፡ ተወሰነና ፡ ወደሱ ፡
አቀረበን ፡ ከቶ ፡ ሃሳባችንን ፡ ሁሉ ፡ አራ
ቀልን ፡ አጋንንትንም ፡ እንዳያውቁ ፡
አደፈጋቸው ።

፲፭ ፤ የማይመረመር የማይለወጥ ፡
ቃል ፡ የሚለወጥ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ
መለወጥ ፡ ይስማማው ፡ የነበረ ፡ ሥጋን
የማይለወጥ ፡ አደረገው ፤ ስለዚህም ፡ በተ
ዋሐደው ፡ በመዋቲ ፡ አዳም ፡ ሥጋ ፡ ተገ
ለጠ ። የማይለወጥ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡
ቃል ፡ የሚለወጥ ፡ ባሕርይ ፡ ባለው ፡
ሥጋ ፡ ሞቶ ፡ በፍዳ ፡ የተያዙትን ፡ አዳ
ናቸው ።

፲፮ ፤ ዕውነተኛ ፡ ትእዛዙንም ፡ ሰጣ
ቸው ፡ ይኸውም ፡ የጌትነቱን ፡ ነገር
የሚናገር ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ከሰ
ውም ፡ የሰይጣንን ፡ ቁራኝነት ፡ አጠፋ ፤
እንግዲህ ፡ በጌታችን ፡ ሞት ሕይወትን
እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ ካለማወቅም ፡ ወደ
ማወቅ ፡ ተሸጋገረን ፡ በማታልፍ ፡ መንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ከን
የመ ፡ ሐኬት ፡ እንንቃ ።

፲፯ ፤ ሰውም ፡ ቢሆን ፡ ቅሉ ፡ እርሱ ፡
ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነው
ሥጋዊ ፡ ልደትን ፡ ለመወለድ ፡ የመጣ ፡
ቀዳማዊ ፡ እርሱ ፡ ከአዳም ፡ የተገኘ ፡
መዋቲ ፡ ሥጋን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ።

፲፰ ፤ አስቀድሞ ፡ በነቢያት ፡ የታወቀ ፡
በሐዋርያት ፡ ስብከትም ፡ የተገለጸ ፡
ፍጥረታት ፡ ሁሉ ፡ የሚያምኑበት ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ አብ ፡ ምስክርነት ፡ የተገለጸ
በመላእክትም ፡ ቃል ፡ የተመሰገነ ፡ ሰው
የሆነው ፡ እርሱ ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡
ነው ።

፲፱ ፤ እኛን ፡ ስለማዳን ፡ በመስቀል ፡
ላይ ፡ ተሰቀለ ። በመስቀሉም ፡ ሕይወ
ትን ፡ አገኘን ። ቤዛችን ፡ ጽንዓችን ፡
እሱ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከእግዚአብሔር
የማትርቅ ፡ መቼም ፡ መች ፡ የማትለይ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ የማትመጠን ፡ የቸርነቱን ፡
ብዛት ፡ በመናገር ፡ የማይፈጸም ፡ ደስታ
ያለበት ፡ ረቂቅ ፡ምሥጢር ፡ ነው ።

፳ ፤ ስለዚህ ፡ ከነዚህ ፡ በላይና ፡ በታች
ከንፈሮች ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ጠንቅቆ
መናገር ፡ አይቻልም ። ምዕመናን ፡ ተመ
ራምረው ፡ የማይደርሱበት ፡ ረቂቅ ፡ ምሥ
ጢር ፡ ነው ። የማይመረመር ፡ ቢሆንም ፡
ቅሉ ፡ ለእነርሱ ፡ የተገለጸ ፡ ሆነ ። መገለጹም
በዓይን ፡ ሊታይ ፡ አይደለም ። በልብ ፡
ሊታሰብ ፡ ነው ፡ እንጂ ። እንግዲህ ፡ እና
መሰግነው ፡ ዘንድ ፡ የምንመካበት ፡ መስ
ቀል ፡ ይህ ፡ ነው ።

፳፩ ፤ እርሱን ፡ በማመን ፡ የሚጠመቁ
ምዕመናን ፡ ፍጹማን ፡ ናቸው ፡ ከሚታይ
ያይደለ ፡ ከተነገረው ፡ ሁሉ ፡ ሰውነታ
ቸውን ፡ በዕውነት ፡ አ ዳ ኑ ። በዚህም ፡
በበጎ ፡ ኅሊና ፡ ጽኑዓን ፡ የም ትሆ ኑ ፡
ራሳችሁን ፡ መርምሩ ፡ አፍአዊ ፡ ጆሮአ
ችሁን ፡ ከፉ ፡ ከመስማት ፡ አፍአዊ ፡ ዓይ
ናችሁን ፡ ከፉ ፡ ከማ የት ፡ ከልክሉ ።

፳፪ ፤ ኢየሱስ ፡ ክ ር ስ ቶ ስ ፡ የሚወደ
ውን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ የደኅንነታችሁ ፡

ንም ፡ ምሥጢር ፡ ታስተውሉ ፡ ዘንድ ፡
እናንት ፡ በክርስቶስ ፡ የምትመኩ ፡ የከበ
ራችሁ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ሕጉን ፡
ያጸናላችሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ያሳደረ
ባችሁ ፡ እናንተ ፡ ና ች ሁ ና ፡ የነፍስን ፡
ሥራ ፡ ሥሩ ፤ ይልቁንም ፡ የሰው ፡ የው
ስጥ ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ያስተውል
ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ወደአባቱ
ሊያቀርበን ፡ ስለፈቀደ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡
መከራ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሲኦል
ወርዶ ፡ የሙታንን ፡ ነፍስ ፡ ለሕይወት
የማረከ ፡ እርሱ ፡ ኢ የ ሱ ስ ፡ ክርስቶስ ፡
ነውና ።

፳፫ ፤ ነፍሳተ ፡ ሲ ኦ ል ን ፡ ለ ማ ው
ጣት ፡ ክርስቶስን ፡ በሥጋ ፡ ወደሲኦል ፡
ሲ ወ ር ድ ፡ ባ የ ው ፡ ጊ ዜ ፡ ሞ ት ፡
በ ታ ላ ቅ ፡ ቃ ል ፡ እ ን ዲ ህ ፡ ሲ ል ፡
ጮኸ ። ሥጋን ፡ ከብልየቱ ፡ አ ድ ሶ ፡
ከመለወጥ ፡ አ ድ ኖ ፡ የ ተ ዋ ሐ ደ ው
ይህ ፡ ማነው ? በኔ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ያለ

ሥጋን ፡ ለብሶ ፡ በባሕርዩ ፡ ያለ ፡ የብር
ሃን ፡ ነፀብራቅ ፡ እኔን ፡ ድል ፡ የ ነ ሣ ፡
ይህ ፡ ማነው ? ።

፳፬ ፤ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ነጥቆ ፡ ይወስደኝ
ዘንድ ፡ በእኔ ፡ ሥ ል ጣ ን ፡ ሥ ር ፡ ካለ
ሥጋ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ይህ ፡
ማነው ? ምድራዊ ፡ ሥጋን ፡ የተዋሐደ ፡
ይህ ፡ ማነው ? እርሱ ፡ ግን ፡ ሰማያዊ ፡
ነ ው ፡ በሚለወጥ ፡ ባሕርይ ፡ የተወለደ
ይህ ፡ ማነው ? እርሱ ፡ ግን ፡ የማይለ
ወጥ ፡ ነው ! ።

፳፭ ፤ ከሕጌ ፡ ል ዩ ፡ የ ሆ ነ ፡ ይ ህ
ማነው ? ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩ ፡ አሕ
ዛብን ፡ ከወገኖቼ ፡ ለይቶ ፡ የሚማርካ
ቸው ፡ ይህ ፡ ማነው ? በነደ ፡ እሳት ፡ ኃይል
ከሞት ፡ ጋር ፡ የሚሰላለፍ ፡ ይህ ፡ ማነው ?
ጨ ለ ማ ን ፡ ድ ል ፡ የ ነ ሣ ፡ ይ ህ ፡
ማነው ? ጨለማን ፡ የተመሉ ፡ መቃብ
ርና ፡ ሲኦል ፡ ይዘው ፡ ሊ ያ ስ ቀ ሩ ት
ያልተቻላቸው ፡ ይህ ፡ ማነው ? ።

፳፮ ፤ በዚህ ፡ እንግዳ ፡ መልክ ፡ በዚህ
ልዩ ፡ ክብር ፡ ያለ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ላደር
ገው ፡ የምፈልገውንም ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣኑ
የምትከለክለኝ ፡ ይህ ፡ ማነው ? ።

፳፯ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ የ ሞ ተ ፡ ይህ ፡
ማነው ? በብርሃኑ ፡ የነጸብራቅ ፡ ኃይል ፡
የጨለማውን ፡ አበጋዝ ፡ ዕውር ፡ ያደረ
ገው ፡ ይህ ፡ ማነው ? ወገኖቼን ፡ እገዛ ፡
ዘንድ ፡ ያልተወኝ ፡ ይህ ፡ ማነው ? ነገር
ግን ፡ ተሰጥተውኝ ፡ የ ነ በ ሩ ት ፡ ነ ፍ ሳ
ትን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያ ወ ጣ ል ፡
እንጂ ።

፳፰ ፡ በሕማም ፡ በሞት ፡ ከሚለወጥ
ባሕርይ ፡ ጋ ር ፡ አ ን ድ ፡ ሆ ኖ ፡ እ ን ዳ
ልቆራኘው ፡ የሚከለክለኝ ፡ ይህ ፡ ሥል
ጣን ፡ ምንድር ፡ ነው ? ልዳስሰው ፡ የማ
ይቻለኝ ፡ ይህ ፡ ማነው ? ሕ ፀ ፅ ፡ የ ሌ ለ
በት ፡ ይህ ፡ ብርሃን ፡ የሚከበው ፡ ማነው ?
ወገኖቼን ፡ እንዳላጠፋ ፡ የሻረኝ ፡ በር

ሱም ፡ ላይ ፡ ሰልጥኜ ፡ የምጎዳው ፡ ሥል
ጣን ፡ የሌለኝ ፡ ይህ ፡ ማነው ? ።
፳፱ ፤ ይህ ፡ የተሰቀለው ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ነው ፤ በግራ ፡ የነበረው ፡ ወደ
ቀኝ ፡ የተዛወረበት ፡ ከታች ፡ የነበረው ፡
ወደ ፡ ላይ ፡ የወጣበት ፤ ከኋላ ፡ የነበ
ረው ፡ ወደፊት ፡ የቀደመበት ፤ በሲኦል
የነበሩ ፡ ነፍሳትን ፡ በልዕልና ፡ ወደገነት
ያወጣቸው ፡ ከማዕርጋቸው ፡ ተዋርደው
የነበሩትን ፡ ወደቀደመ ፡ ክብራቸው ፡ የመ
ለሳቸው ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ነው ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ፤ እ ር ሱ ፡ ኢ የ ሱ ስ ፡ ክርስቶስ ፡
ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተ ነ ሥ ቶ ፡ ወ ደ ፡
ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ የሲኦልን ፡ የብረት ፡
መዝጊያ ፡ ሰብሮ ፡ በሞቱ ፡ ሞትን ፡ ደመ
ሰሰው ፤ አጠፋው ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን
ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡
አባት ፡ ሆይ ፤ የአምላክ ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡
የተከናወነና ፡ የተቀላጠፈ ፡ ነው ፡ አመሰ

ግንሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ሥግው ፡ ቃል ፡ አባ
ቱን ፡ አመሰገነ ።
፪ ፤ አባት ፡ ሆይ ፡ የማመሰግንህም ፡
በእሊህ ፡ በሥጋውያን ፡ ከና ፍ ር ፡ አይ
ደለም ፤ ዕውነትና ፡ ሐሰት ፡ በሚነገር
ባት ፡ በዚች ፡ አንደበትም ፡ አይደለም
ከሥጋዊ ፡ ባሕርይ ፡ በሚገኝ ፡ በ ዚ ህ ፡
ቃልም ፡ አይደለም ፡ ንጉሥ ፡ ከአንተ ፡
ተገኝቶ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ በሚታወቅ ፡
በዚህ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፫ ፤ ስለሆነም ፡ ወደ ፡ ሥጋዊ ፡ ጆሮ ፡
የማይገባ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ባለ ፡
በሚነገር ፡ ቃል ፡ አይደለምና ።
፬ ፤ ከአንተ ፡ ተገኝታ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ
በተፈጠረባት ፡ ቃል ፡ በአንተና ፡ በኔ ፡ ህል
ውና ፡ ባለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልውሆና
የሚናገር ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፭ ፤ አባት ፡ ሆይ ፤ ራ ስ ህ ፡ የ ም ት
ወደድ ፡ ራስህ ፡ የምትመሰገን ፡ አንተ ፡
አብ ፡ ነህና ፡ ፍጹማን ፡ ከ ቡ ራ ን ፡ የሚ

ሆኑ ፡ የምዕመናን ፡ ወ ገ ና ች ፡ ሁሉ ፡
ወዳንተ ፡ የሚጸልዩበት ፡ ገንዘብ ፡ ነህ ፡
፮ ፤ አባት ፡ ሆይ ፤ ወ ዳ ጅ ፡ አንተን
ይጠራሉ ፡ አባት ፡ ሆይ ፤ መጋቢ ፡ አንተን
ረዳት ፡ አንተን ፡ ይጠራሉ ።
፯ ፤ የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ሁሉ ፡ በአንተ ፡
ቃል ፡ ተፈጥሯልና ፡ ሁሉ ፡ ላ ን ተ ፡ ይገ
ዛል ፤ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበርክ ፡ ከአ
ንተ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ የለምና ።
በዕውነት ፡ ለዘለዓለም ፡ የም ት ኖ ር ፡
አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ።
፰ ፤ እንግዲህ ፡ ጠባቂው ፡ ወ ይ ም ፡
መምህሩ ፡ የምሥጢራትን ፡ ነገር ፡ ይገ
ልጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ ከመጸለዩና ፡
ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ እንድታውቁ ፡ እን
ድትረዱ ፡ ጠባቂው ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማ
ያትን ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ
ይገባዋል ፡ ሲል ፡ ኢ የ ሱ ስ ፡ ተናገረ ።
፱ ፡ በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ የተዘመዱት ፡
በጸሎተ ፡ ቅዳሴም ፡ ስሙን ፡ የሚጠሩት ፡

ማን ፡ እንደሆነ ፡ በዕዝነ ፡ ልቡናቸው ፡
ቢያውቁ ፡ ቢረዱ ፡ ይጠቀማሉና ።
፲ ፤ ዳግመኛም ፡ አዲሶች ፡ አማኞችን
እናንተ ፡ ወንድሞች ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ቀርባችኋል ፤ በእርሱ ፡ ብቻ ፡ እም
ናችሁ ፡ ጸንታችሁ ፡ እንዳላችሁ ፡ አው
ቃችኋል ፡ ይበላቸው ።
፲፩ ፤ እርሷን ፡ ይሰጣችሁና ፡ የተና
ገራት ፡ ሃይማኖትንም ፡ ገንዘብ ፡ ታደር
ጓት ፡ ዘንድ ፡ ይህችውም ፡ ዓይን ፡ ያላያት
ጆሮ ፡ ያልሰማት ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ያል
ታሰበች ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚወዱት ፡
ብቻ ፡ ያዘጋጃት ፡ ናት ።
፲፪ ፤ ሙሴና ፡ ሌሎችም ፡ ቅዱሳን ፡ ነቢ
ያት ፡ ሃይማኖት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገን
ዘብ ፡ መሆኗን ፡ ነግረውናልና ፡ አስተም
ረዋልና ፡ እኛም ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ጽንዕ
ለዘላለሙ ፡ ለሱ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡
በዕውነት ፡ እናምናለን ፡ ለዘለዓለሙ ፡
አሚን ።

ሕማማተ ፡ መስቀል ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ መጻሕፍትን ፡ እንዲጀምሩ ፡ በአብ ፡ ስም ፡ ወላዲ በወልድ ፡ ስም ፡ ተወላዲ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ሠራፂ ፡ ምንም ፡ ለአጠይቆ አካላት ፡ በስም ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ ብንል፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ በማመን ፡ ሕማማተ ፡ መስቀሉን ፡ ለመጻፍ ፡ እንጀምራለን ። ሕማማተ ፡ መስቀል እንዴት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ጌታችን ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለኛ ፡ ብሎ ፡ ታመመ ፡ ተሰቀለ ፡ ሞተ ፤ ሐመ ፡ በእንቲአነ፡ወሞተ ፡ በእንቲአነ ፡ ሞተ ፡ በፈቃዱ ፡ ወተቀብረ ፡ በሥምረቱ ፡ እንዳለ ፡ መጽሐፈ ፡ ሊቃውንት ።

መታመሙም ፡ በሰውነቱ ፡ እንጂ ፡ በመለኮቱስ ፡ ርኁቅ ፡ እምቅንዋት ፡ ጥዑይ ፡ እምሕማማት ፡ ነው ፡ ሐማሚ ፡ በትስብእቱ ፡ ኢሐማሚ ፡ በመለኮቱ ፡